
መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
Kidst Slassie Ethiopian Orthodox Tewahido Church
የ መልእክት ሳጥን ቁጥር ፡ P.O. Box 42204 Arlington, VA 22204 (703) 606-1976


**‹‹...ተላላፊዎች ሆይ፥ ንስሐ ግቡ፥ ልባችሁንም መልሱ።››**
ኢሳ46 ፥8

# ንስሐ

**ንስሐ ዋና የቃሉ ትርጉም በሙሉ ልብ የአሳብ መለወጥና መመለስ ማለት ነው። አሳብ ከተለወጠ አድራጎተ ይለወጣል። በዚህ ቃል ነቢያት ሕዝቡን ያስጠነቅቁ ነበር**

ኢሳ. 46 ፥ 8

"8፤ ይህን አስቡና አልቅሱ፤ ተላላፊዎች ሆይ፥ ንስሐ ግቡ፥ ልባችሁንም መልሱ።"

ሕዝ. 18 ፥ 30

"30፤ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ስለዚህ እንደ መንገዱ በየሰዉ ሁሉ እፈርድባችኋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ንስሐ ግቡ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ።"

**የዮሐንስና የጌታችን የትምህርት መጀመሪያ ‹‹ንስሐ ግቡ›› የሚል ነው፡፡**

ማቴ. 3 ፥ 1፡2

"1-2 በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ። መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ።"

ማቴ. 4 ፥ 17

"17 የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ። ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ። መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር።"

**ንስሐ የሚገባ ስለ ኃጢአቱ አሳቡ ሁሉ ይለወጣል። መጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢአቱ ይወቅሰዋል።**

ዮሐ. 16 ፥ 8

"8 እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤"

**ከኃጢአቱ ይመለሳል ይቅርታም ይጠይቃል።**

መሳ. 28 ፥ 13

"13 ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል።"

ሉቃ. 15 ፥ 11-24

"11 እንዲህም አለ። አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት።
12 ከእነርሱም ታናሹ አባቱን። አባቴ ሆይ፥ ከገንዘብህ የሚደርሰኝን ክፍል ስጠኝ አለው። ገንዘቡንም አካፈላቸው።
13 ከጥቂት ቀንም በኋላ ታናሹ ልጅ ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ሩቅ አገር ሄደ፥ ከዚያም እያባከነ ገዘቡን በተነ።

14 ሁሉንም ከከሰረ በኋላ በዚያች አገር ጽኑ ራብ ሆነ፥ እርሱም ይጨነቅ ጀመር።
15 ሄዶም ከዚያች አገር ሰዎች ከአንዱ ጋር ተዳበለ፥ እርሱም እሪያ ሊያሰማራ ወደ ሜዳ ሰደደው።
16 እሪያዎችም ከሚበሉት አሰር ሊጠግብ ይመኝ ነበር፥ የሚሰጠውም አልነበረም።
17 ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ። እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ
እጠፋለሁ።
18 ተነሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና። አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥
19 ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ።
20 ተነሥቶም ወደ አባቱ መጣ። እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፥ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው።
21 ልጁም። አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም አለው።
22 አባቱ ግን ባሪያዎቹን አለ። ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፥ ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ
ስጡ፤
23 የሰባውን ፊሪዳ አምጥታችሁ እረዱት፥ እንብላም ደስም ይበለን፤
24 ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም። ደስም ይላቸው ጀመር።"

## እውነተኛ ንስሐ ከዓለማዊ ጸጸት የተለየ ነው።

2 ቆሮ. 7 ፥ 10

"10 እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን ጸጸት የሌለበትን፥ ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንስሐ ያደርጋልና፤ የዓለም
ኀዘን ግን ሞትን ያመጣል።"

## በሥራም ለውጥ ይታያል

ማቴ. 3 ፥ 8

"8 እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤"

የሐዋ. 26 ፥ 20

"20 ነገር ግን አስቀድሜ በደማስቆ ላሉት በኢየሩሳሌምም በይሁዳም አገር ሁሉ ለአሕዛብም ንስሐ ይገቡ ዘንድና ለንስሐ
የሚገባ ነገር እያደረጉ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ ተናገርሁ።"

## ሰው ንስሐ ሲገባ ኃጢአቱ ይሰረያል ይደመሰሳልም

የሐዋ. 2፤38

"38 ጴጥሮስም። ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ
ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።"

የሐዋ. 3፤19

"19-20 እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን
እንዲልክላችሁ፥ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም።"

## ንስሐ መግባት የመዳን መጀመሪያ እርምጃ ነው፤ ከእምነትም ጋር የተያያዘ ነው

ማር. 1 ፥ 14

"14-15 ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከና። ዘመኑ ተፈጸመ
የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ።"

የሐዋ. 2 ፥ 38

"38 ጴጥሮስም። ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ
ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።"

የሐዋ. 20 ፥ 20

"20-21 ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ንስሐንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን ለአይሁድና ለግሪክ ሰዎች እየመሰከርሁ በጉባኤም

*በየቤታችሁም አወራሁላችሁና አስተማርኋችሁ እንጂ፥ ከሚጠቅማችሁ ነገር አንዳች ስንኳ አላስቀረሁባችሁም።"*

## ሰዎች ሁሉ ንስሐ እንዲገቡ ታዝዘዋል ለንስሐም ጊዜ ተሰጥቶአቸዋል

*የሐዋ. 11 ፥ 18*

*"18 ይህን በሰሙ ጊዜም ዝም አሉና። እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሐን ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ።"*

*የሐዋ. 17 ፥ 30*

*"30 እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤"*

*2 ጴጥ. 3 ፥ 9*

*"9 ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።"*

## አማኝ ኃጢአትን ሲሠራ ቶሎ ንስሐ እንዲገባ ታዝዞአል

*ራእ. 2 ፥ 5*

*"5 እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ።"*

*ራእ. 2 ፥ 16*

*"16 እንግዲህ ንስሐ ግባ፤ አለዚያ ፈጥኜ እመጣብሃለሁ፥ በአፌም ሰይፍ እዋጋቸዋለሁ።"*

*ራእ. 2 ፥ 21*

*"21 ንስሐም እንድትገባ ጊዜ ሰጠኋት ከዝሙትዋም ንስሐ እንድትገባ አልወደደችም።"*

*ራእ. 3 ፥ 19*

*"19 እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ።"*

## ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ቸል ካለ በኋላ እንዲሁ ሲመቸው ንስሐ ሊገባ አይችልም። ንስሐ የእግዚአብሔር ስጦታ ነውና

*2ጢሞ. 2 ፥ 25*

*"25-26 ደግሞም። ምናልባት እግዚአብሔር እውነትን ያውቁ ዘንድ ንስሐን ይሰጣቸዋልና ፈቃዱን ለማድረግ በዲያብሎስ ሕያዋን ሆነው ከተያዙበት ወጥመድ ወጥተው፥ ወደ አእምሮ ይመለሳሉ ብሎ የሚቃወሙትን በየዋህነት ይቅጣ።"*

*ዕብ. 6 ፥ 4-6*

*"4 አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን*
*5 መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን*
*6 በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፤ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና ያዋርዱትማልና። "*

*ዕብ.12 ፥ 17*

*"17 ከዚያ በኋላ እንኳ በረከቱን ሊወርስ በወደደ ጊዜ እንደ ተጣለ ታውቃላችሁና፤ በእንባ ተግቶ ምንም ቢፈልገው ለንስሐ ስፍራ አላገኘምና።"*

*ምንጭ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት*